# የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መርሐግብር

መጋቢት 2009 ዓ.ም.

# ማውጫ

ማውጫ....................2
ክፍል አንድ.................... 3
መግቢያ....................3
ክፍል ሁለት፦ አጠቃላይ መርሆዎች ....................6
ራዕይ፦ ....................7
ዕሴቶች፦....................7
ክፍል ሦስት፦ ዓላማና ተልዕኮ....................7
3. 1 ዓላማ ....................7
3.2 ተልዕኮ ....................7
ክፍል አራት ግብ፦....................7
ክፍል አምስት፦ ስልት....................8
ክፍል ስድስት፦ ርዕዮተዓለምና ፖለቲካዊ አቋም....................9
6.1 ርዕዮተዓለም፡....................9
6.2 ፖለቲካዊ አቋም፦ ....................9
6.3 የመንግሥት ቅርጽና ተግባር፦ .................... 10
ክፍል ሰባት፦ የዜጎች መብቶች፦ ....................11
7.1 ሰብአዊ መብቶች፦ ....................11
7.2 ዴሞክራሲያዊ መብቶች፦....................12
7.3 የሃይማኖት ነፃነትና ዕኩልነት፦....................12
7.4 የነገዶችና የጎሣዎች ዕኩልነት፦....................12
ክፍል ስምንት፦ የኢኮኖሚ ጉዳዮች፦....................13
ክፍል ዘጠኝ፦ ማኅበራዊ ጉዳዮች፦....................15
9.1 የትምህርት ፖሊሲ፦....................15
9.2 የጤና ፖሊሲ፦....................15
9.3 የባህል ፖሊሲ፦....................16
9.4 ማኅበራዊ ዋስትና፦....................16
ክፍል አሥር፦ የሀገር መከላከያና የሕዝብ ደህንነት፦....................16
ክፍል አሥራ አንድ፦ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፦....................17

# ክፍል አንድ፡-

## *መግቢያ*

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሚባሉትና የራሳቸውን የፀና መንግሥት መሥርተው በሕዝብ አስተዳደርና በሥልጣኔ ቀደምት ከነበሩት ሀገሮች አንዷ እንደሆነች የዓለም ታሪክ ያረጋገጠው ዕውነታ ነው። ምንም እንኳ የመልክዓምድር ክልሏ በተለያዩ ጊዜአት ሲሰፋና ሲጠብ የነበረ ቢሆንም፣ ከሦስት ሺህ ዘመን በላይ የታወቀ ክልል እና የፀና መንግሥት የነበራትና ለሌላው ዓለም ሊተላለፍ የቻለ የሥልጣኔ ምንጭ ሀገር እንደሆነች ታሪክ እና የሥነ ምድር-ቅሬተ አካል የምርምር ውጤቶች ያሳያሉ። በኢትዮጵያ ረጅም የታሪክ ዘመን፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥታት ውስጥ በአስተዳደር፤ በሥልጣንና በሥራ ድርሻ ክፍፍል ላይ እንደወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነገድና ጎሳ የተካፈሉበት እንደነበር የአገሪቱ አንድነት ለረጅም ዘመን ፀንቶ መዝለቁ ሕያው ምሥክር ነው።

ከሁሉም በላይ፣ የኢትዮጵያ አንድነት፣ ነፃነት፣ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ተጠብቆ እንዲዘልቅ፣ በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘኖች የክብር ዘብ ሆነው ከኖሩት የኢትዮጵያ ነባር ነገዶችና ጎሳዎች መካከል፣ ዐማራው አንዱና ግንባር ቀደሙ እንደሆነ ማንም ይስተዋል የሚባል አይደለም። በመሆኑም ዐማራው በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ውስጥ በሁሉም መስኮች፣ ማለትም፡- በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ኑሮ እና በአገር መከላከያ የበኩሉን የጎላ አስተዋጽኦ አድርጓል። ሀገሪቱን ከውጭ ከሚመጡ ወራሪዎች ለመጠበቅ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ነገዶችና ጎሳዎች ጋር በመሆን ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ የሕይዎት፣ የአካል እና የገንዘብ መስዋዕትነት ከፍሏል። ይህም በመሆኑ፣ ዐማራው ከኢትዮጵያዊነት ጋር የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች የሆነ ማንነትን የገነባ ሕዝብ ለመሆን የበቃ ነው። ዐማራው በአሰፋፈር ረገድ በግራኝ እና በኦሮሞ የተራዘመ ወረራ ምክንያት፣ ከምሥራቅ፣ ከደቡብ ምዕራብና ከደቡብ ኢትዮጵያ ተገፍቶና ማንነቱን ተነጥቆ፣ በመሀል፣ በሰሜንና በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በብዛት እንዲኖር ቢገደድም፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች (ጠቅላይ ግዛቶች) በከፍተኛ ደረጃ ተሰራጭቶ የሚገኝ ታላቅ ሕዝብ ነው። ለወደፊቱም ኅልውናውን አስከብሮ፣ ኢትዮጵያዊነቱን ለድርድር ሳያቀርብ፣ በማንነቱ ፀንቶ የሚኖር ሕዝብ ነው።

ይኸም ሆኖ፣ ዐማራው በኢትዮጵያ በነበሩት የአገዛዝ ሥርዓቶች ሁሉ፣ በሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሱና የተፈፀሙ ጭቆናዎችንና ግፎችን እንደ ሕዝብ አብሮ ሲቀበል ኖሯል። ስለዚህ ሮማን ፕሮቻስካ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በሰበከው ፀረ-ዐማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ የተለከፈው የግራው የዓለም አመለካከት ትውልድ እንዳራመደው ሳይሆን፣ ከሌሎች ተነጥሎ ተጠቃሚም፣ ገዥም እንዳልነበር የሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አስረጅ ነው። ስለሆነም፣ የዐማራው ነገድ በተለያየ ጊዜ በነበሩ የአገዛዝ ሥርዓቶች፣ እንደማናቸውም የኢትዮጵያ ነገዶችና ጎሳዎች «ነበሩ» የተባሉትን ጭቆናዎችና ግፎች ተቀብሏል። ይልቁንስ ጨቋኝና አፋኝ አገዛዞችን ለማስወገድም በተደረጉ ሕዝባዊና ቡድናዊ እንቅስቃሴዎች ግንባር ቀደም በመሆን ታግሏል፣ መስዋዕትነትም ከፍሏል። ለአብነት ያህል በዐፄ ኃይለሥላሴ የአገዛዝ ዘመን የነደጃዝማች ታከለ ወልደሐዋርያት እና የእነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ያልተሳኩ የመፈንቅለ

መንግሥት ሙከራዎችና በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የዐማራው ነገድ ልጆች የግንባር ቀደምትነቱን ሚና መጫዎታቸው የሚዘነጋ አይደለም።

የዐማራው ነገድ የኢትዮጵያን ኅልውና ለማስጠበቅ ግንባር ቀደምት ከመሆን አልፎ፣ ወሣኝ  እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁት የውጭ ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥ ኃይሎች፣ ኢትዮጵያን በፈለጓት መልኩ ከእጃቸው ለማድረግ፣ ቀድመው ማጥፋት ያለባቸው የዐማራውን ነገድ ማንነት መሆኑን ካመኑ ቆይተዋል። ለዚሁ ዓላማቸው ዕውን መሆን ሠፊና ጥልቅ ዕቅድ ነድፈው መንቀሳቀሳቸውን ታሪካችንና የምንገኝበት ሁኔታ ያስረዳል። ጣሊያን ካንድም ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛቱ ለማድረግ አቅዶ ሲንቀሳቀስ፣ ይህንን ዕቅዱንም ለማስፈፀም ሲል የትግሉ ስልት አድርጎ የተነሳው የዐማራውን ነገድ ነጥሎ በማጥፋት ወይም በማዳከም ሀገሪቱን በፍላጎቱ ሥር ማዋል ነበር። ለዚህም ይረዳው ዘንድ፣ የአገሪቱን አስተዳደር በነገድ ከፋፍሎ፣ እርስ በርሳቸው በጠላትነት በመተያየት፣ «ኢትዮጵያዊ» የሚያሰኙዋቸውን የጋራ መታወቂያ ማንነቶችንና ዕሴቶችን በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ እንደነበር ይታወቃል። በዚህ ዕቅዱ መሠረትም ለአምስት ዓመት በከተሞች ዙሪያ በቆየባቸው  ጊዜያቶች ውስጥ «ኢትዮጵያ» የሚለውን የሀገራችንን ጥንታዊ መጠሪያ ስም ሰርዞ፣ «የምሥራቅ አፍሪካ የጣሊያን ቅኝ ግዛት አስተዳደር» በሚል ተክቶት እንደነበር ይታወሳል። የውስጥ አስተዳደሩንም፦ «ትግራይ-ትግርኝ፣ ዐማራ፣ ጋላ[ኦሮሞ]-ሲዳማ፣ ሸዋ፣ ሐረር እና ሶማሊ» ብሎ በመክፈል፣ መግባቢያ ቋንቋቸውን በተከታታይ “ትግርኛ፣ ዐማርኛ፤ ጋልኛ[ኦሮምኛ] እና ከፋቾኛ፣ ዐማርኛ፣ ዐረብኛና ሱማልኛ” እንዲሆን አደረገ። በዚህ ክፍፍል መሠረትም ዐማራው ማንነቱን፣ ባህሉን፣ ሃይማኖቱንና ትውፊቱን እንዲያጣ ብዙ ርቀት ተጉዟል። በገፍ እና በግፍ ተገደለ። «ጋላ[ኦሮሞ]-ሲዳማ» እና «ሐረር» ብሎ በከለለው ክፍል ይኖሩ የነበሩ ዐማሮችን ነጥሎ ተወልደው ካደጉበትና ከእርስታቸው በመንቀል ሀብት ንብረታቸውን ነጥቆ ከአካባቢው እንዲባረሩ በማድረግ የዘር ማጽዳት ወንጀል ፈጸመ። ዛሬ የትግሬ ወያኔ ነፃ አውጭ ቡድን በወቅቱ የእርሱ አጋር ከነበረው ኦነግ ጋር እየተመሳጠረ በተለይ ዐማራውን በማግለልና በጠላትነት በመፈረጅ ለእርሱ በሚያመቸው ሁኔታ አገሪቱን  በዘጠኝ የጎሣ «መንግሥታት»  ከፋፍሎ በዐማራው ነገድ ላይ እየፈፀመ ያለው የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል ዘመቻ፣ በኢትዮጵያ አርበኞች ከሽፎ የነበረው የምዕራባውያን ዐማራን የማጥፋት ታላቅና ተከታታይ  ዕቅድ አካል መሆኑን ድርጊቱ በግልፅ ያሳያል።

የአሁኑ ዘመን የትግሬ ወያኔዎችም ፋሺስት ጣሊያን ባቀደው መሠረት ሀገሪቱ በጎሳ እንድትከፋፈል ሲያደርጉ የሐሰት ታሪክ በመፍጠር ሌሎች ጎሳዎች ውስጥ የሚመጡ ጥቂት ምሑራን የዐማራ ጥላቻ እንዲያድርባቸውና በዐማራው ላይ እንዲነሱ አድርገዋል። ከሁሉም በላይ የትግሬ-ወያኔ በፕሮግራሙ ፀረ-ዐማራ ብቻ ሳይሆን፣ «ዐማራን ከምድረ-ገጽ ካላጠፋ፣ የትግራይ ሕዝብ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም» ሲል ያሰፈረውን ተግባራዊ ለማድረግ ላለፉት አርባ ዓመታት በስፋት ተንቀሳቅሷል። በመሆኑም በመላ ሀገሪቱ ተሰራጭቶ ይኖር የነበረው ዐማራ፣ ላለፉት 26 ዓመታት የጥቃት ሰላባ እንዲሆንና እንዲገደል፣ ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆን፣ ንብረቱ እንዲወረስ እና እንዲሳደድ ተደርጓል። በሌላ በኩልም በዐማራው መካከል ሳይቀር፣ «ጨቋኝና ተጨቋኝ» በማለት እንዲከፋፈልና እርስ በራሱ እንዲተላለቅ አድርጓል። በትግሬ-ወያኔ አስተዳደር ውስጥ ያለው የጠቅላይ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ያመነውን ብቻ እንኳን ብንወስድ 2.4 ሚሊዮን ዐማራ ከምድረ ኢትዮጵያ እንዲጠፋ መደረጉን አልሸሸገም። በጥቅሉ በትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር የ26 ዓመታት አገዛዝ ከ5 ሚሊዮን በላይ ዐማሮች ከምድር ገጽ እንዲጠፉ መደረጉን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ወያኔ በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ዐማራው እንዳይዋለድ የዐማራ እናቶች በወሊድ መከላከያ ስም አምካኝ እንክብሎች በመስጠት መካንና ታማሚ እንዲሆኑ አድርጓል። የዐማራ ሴቶችን ማምከን ብቻ ሳይሆን ወንዱንም አኮላሽቷል፤ የኤች አይቪ ቫይረስን በመርፌ አሰራጭቶ ሕዝቡን ሚችና ታማሚ አድርጓል።

ስለሆነም የትግራይ ወያኔ ነፃነት ግንባር አገዛዝ፥ ዐማራው ንብረት እንዳያፈራ፣ ከማናቸውም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውጭ እንዲሆን አድርጓል። ለዘመናት ያፈራውን አንጡራ ሀብቱንና እርስቱን እንዲወረስ፣ እንዲነጠቅ፣ እንዲሳደድ አድርጓል።

ሕዝቡን አናሳ፣ በማንነቱ የሚያፍርና የሚሸማቀቅ ለማድረግ፣ የሕዝቡን ማንነት፣ ባህልና ወግ ለማጥፋት ተንቀሳቅሷል። ቀደም ሲል በዐማራነታቸው በጎንደር ጠቅላይ ግዛት ሥር ይተዳደሩ የነበሩት የወልቃይት፣ የጠገዴና የጠለምት ወረዳዎች፤ እንዲሁም በወሎ የራያና ቆቦ ወረዳ ወደ ትግራይ እንዲካተቱ በማድረግ፣ ዐማራዊ ማንነታቸውን በትግሬ ማንነት በግድ እንዲለውጡ፣ እጅግ መጠነ ሠፊ የሆነ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጫናዎች እየፈጸመባቸው ይገኛል። ወያኔ በዚህ ለም መሬቶችን ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በትግሬ ቁጥጥር ስር ለማድረግ በተያያዘው አባዜ፣ ራሱ «የዐማራ ነው» ብሎ በከለለው ክልል ሳይቀር «የዐማራው ድርሻ ነው» የተባለውንም ግዛት ለሌሎች እንዲታደል አድርጓል።

ከጎጃም ክፍለ-ሀገር ግማሽ ያህል የቆዳ ስፋት የሚይዘውን ብዙ ዐማራ የሚኖርበትን የመተከልን አውራጃ «ቤንሻንጉል-ጉምዝ» ብሎ ሌላ አዲስ ግዛት ፈጥሯል። ይህ ዓይነቱ ተግባር እጅግ በከፋ ሁኔታ በሸዋ ክፍለሀገር ውስጥ ይኖሩ በነበሩ ዐማሮችና መሬቶች ላይ ተፈጽሟል። «ሸዋ» ተብሎ ይታወቅ የነበረው መካከለኛው የኢትዮጵያ ግዛት፣ ዛሬ በትግሬ-ወያኔዎች አገዛዝ፥ አዲስ አበባ፣ ደቡብ ክልል፣ ኦሮሚያ እና ሰሜን ሸዋ በሚባሉ ትናንሽ ግዛቶች ተቀይሯል። በጥቅሉ የትግሬ-ወያኔ የዐማራው ነገድ በቁጥር አናሳ የሚሆንበትን፣ በፖለቲካው ዘርፍ የማይሳተፍበትን፣ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚገደብበትን፣ በማኅበራዊ ኑሮም በሌሎች ነገዶች የሚገለልበትን፣ በአጠቃላይም በሀገሪቱ ውስጥ ሠርቶና ተዋልዶ እንዳይኖር የሚያደርገውን ሥርዓት መሥርቷል።

ዐማራው በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደር በመሆኑ፣ ይህ ሁሉ ጥቃት እየደረሰበት፤ ዐማራዊ ማንነቱንና ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ለድርድር የማያቀርብ መሆኑን በትግሉ እያስመሰከረ ይገኛል። የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር፣ ገና ከጅምሩ በፖለቲካ ፕሮግራሙ ውስጥ ዐማራውንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በጠላትነት ፈርጆ በሰነድ አስቀምጧል። በዚያም መሠረት የትጥቅ ትግል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁንም የማዕከላዊ መንግሥት አስተዳደርን ከያዘ በኋላ «የዐማራ ክልል» ብሎ ለራሱ በሚመች መልኩ በከለለው ግዛት ውስጥ በአምሳሉ የፈጠራቸውን ሰዎች ለይስሙላ አስቀምጦ በዐማራው ላይ የዘር ማጥፋት ተግባር እንዲፈፀምበት አድርጓል፤ እየፈፀመበትም ይገኛል። የኢኮኖሚ ተጎጂ በማድረግ የበይ ተመልካች እንዲሆን አድርጎታል። ዐማራ የሆኑ ሀገር-አውል አባቶችና ጎልማሶችን በረጅም ጊዜ የሥራ ልምዳቸውና ዕውቀታቸው ያገኙትን አስተሳሰብ ለተከታዩ ትውልድ እንዳያስተላልፉ፣ "አድሐሪ፣ ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ፣ የድሮ ሥርዓት ናፋቂ" ወዘተርፈ . . . . የሚሉ የስም ማጥፊያ መጠሪያዎች በመለጠፍ፣ ከሁሉም ነገር እንዲገለሉ አድርጓል። በሌላ በኩል የዐማራውን ነገድ ለመጉዳት ከመፈለግ የተነሳ የኢትዮጵያ ወሰን የሆነውን መሬት ለሱዳን ሰጥቷል። የሱዳን ወታደሮችም የኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው በመግባት የዐማራ ገበሬዎችን እንደገደሉና ንብረታቸውንም እንደወረሱ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ዛሬ፣ የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ያንገፈገፋቸው ዐማሮችም በእምቢተኝነት መሣሪያ አንስተው በመፋለም እየሞቱም እየገደሉም ይገኛሉ። በጎንደር እና በጎጃም ብዙ ወጣቶች ለነፃነታቸው ሕይወታቸውን በመሰዋት ላይ ይገኛሉ። በተለያዩ አካባቢዎች ዐማራ ለኅልውናው ሲል ተጋድሎውን እያጠናከረ ይገኛል። በአንድ በኩል ይህ ዐማራው ለኅልውናው የሚያደርገው ተጋድሎ ግቡን እንዲመታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዘላቂነት የዐማራውን ነገድ ከጥፋት ለመታደግና የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ፣ ተጋድሎው የላቀ ድርጅትና አመራር ባለቤት ይሆን ዘንድ ጊዜው ጠይቋል።

በመሆኑም ይህን ጊዜው ለጠየቃቸው የዐማራ ነገድ ከፍተኛ የኅልውና አደጋና የኢትዮጵያ ሀገራዊ ቀጣይነት ሁለት ወሳኝ ፈተናዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ሲባል ቀጣዩን ትግል በሁለት ተከታታይ ምዕራፎች በቅደም ተከተል ከፋፍሎ የትግሬ ወያኔን ጎሠኛና ጨካኝ ቡድን በቆራጥንት መታገል የግድ ብሏል። የመጀመሪያውና ወሳኙ የትግል ምዕራፍ፣ የዐማራን ነገድ ከፍፅም ጥፋት በመታደግ ኅልውናውን ማስከበር ነው። ሁለተኛው በዚህ ጠንካራ መደላድል ላይ ተምሥርቶ፣ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ነገዶችና ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አደጋ ላይ እየወደቁ ያሉትን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ማስከበር ናቸው። ለዚህም ያመች ዘንድ መሪ ድርጅት መመሥረት የግድ በመሆኑ "የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት" (ዐኅኢአድ) የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት ተመሥርቷል።

እነዚህን ሁለት ተያያዥና ተደጋጋፊ የሆኑ የትግል ምዕራፎችን ደረጃ በደረጃ በድል ለመደምደም እንዲቻል ይህ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል። ፕሮግራሙ ያካተታቸው አርዕስቶችም የሚከተሉት ናቸው:- አጠቃላይ መርሆዎች፣ ራዕይ፣ ዕሴቶች፣ ዓላማና ተልዕኮ፣ ግብ፣ ሥልት፣ ርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካዊ አቋም፣ የመንግሥት ቅርጽና ተግባር፣ የዜጎች መብት፣ የኢኮኖሚ ጉዳዮች፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ የሕዝብ ደኅንነትና የአገር መከላከያ፣ እና የውጭ ጉዳይ ናቸው።

# ክፍል ሁለት፡- አጠቃላይ መርሆዎች

የሚከተሉት አጠቃላይ መርሆዎች ዐኅኢአድ የሚያምንባቸውና ለተግባራዊነታቸው የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያደርግባቸው ይሆናሉ:-

2.1 ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት መታደግ።

2.2 በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዐላዊነት ላይ የፀና አቋም አለው፤ ለድርድርም መቅረብ የለበትም ብሎ ያምናል።

2.3 በሀገሪቱ ውስጥ የግለሰብ መብቶች እስከተከበሩ ድረስ የወል መብቶች ይከበራሉ ብሎ ያምናል። ለዚህም በፅናት ይታገላል። ከኢትዮጵያ የመገንጠልን ጥያቄ በፅኑዕ ይቃወማል።

2.4 የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለምንም ገደብ መከበር እንዳለባቸው ያምናል። ለእነርሱም ተግባራዊነት በርትቶ ይታገላል።

2.5 ዜጎች በፈለጉት ቦታ ተንቀሳቅሰው የመሥራት፣ ሀብት የማበጀት፣ ደስታን የመፈለግ፣ በነፃነት ሐሳባቸውን የመግለፅ መብታቸው በሕግ የተከበረ እንዲሆን ይታገላል።

2.6 ዜጎች የሚፈልጉትን የፖለቲካ ፓርቲ ያለምንም ተጽእኖ የመደገፍ መብታቸው በሕግ የተከበረ እንዲሆን ይታገላል።

2.7 ዜጎች በሕዝብ ተመራጮች ላይም ሆነ በመንግሥት ላይ ተቃውሞ የማቅረብ መብታቸው በሕግ እንዲከበር ይታገላል።

2.8 ዜጎች እራሳቸውንም ሆነ ንብረታቸውን ከማንኛውም ጥቃት ለመከላከል የጦር መሣሪያ የመያዝ መብታቸው የተከበረ እንዲሆን ይታገላል።

2.9 ዐኅኢአድ ዜጎች ለመሬት ባለቤትነት እንዲበቁ ይታገላል። ዜጎች በግል የያዙትን መሬት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስና በወለድ አገድ የማስያዝ መብት እንዲኖራቸውና ይህም መብታቸው በሕግ እንዲከበር ይታገላል።

2.10 የኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና የግዛት አንድነት፣ ዳር ድንበሮቿ፣ በዘመነ ትግሬ-ወያኔ ብሔራዊ ጥቅሟን በሚጎዳ መልኩ በሁለትዮሽና በጋርዮሽ የተዋዋለቻቸው ውሎችና ስምምነቶች፣ የተበደረቻቸው ዕዳዎች፣ የተዘረፈ የሀገር ሀብት በተመለከተ፣ የሀገራችን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም በሚያስከብር መልኩ እንዲሆን ይታገላል።

## ራዕይ፡-

የዐማራው ኅልውና በአስተማማኝ ሁኔታ ተከብሮ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ነን ብለው ከሚያምኑ ነገዶችና ጎሳዎች ጋር ተባብሮና ተደጋግፎ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ተከብሮ፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕዝቡ መሪውን እየመረጠ አንድነቱ፣ ሰላሙና ብልፅግናው ተከብሮ ማየት።

## ዕሴቶች፡-

ነፃነት፣ ፍትሕ፣ ሃይማኖት፣ መከባበርና መረዳዳት፣ ታማኝነት፣ ተስፋ፣ ቁርጠኝነት፣ ጽናት፣ ጀግንነት፣ መስዋዕትነት፣ ቤተሰባዊ ፍቅር፣ ርስት (የግል ሀብት)፣ በሥራ ልቆ መገኘት፣ ለሕግ ተገዢ መሆን፣ የአገር ፍቅር እና በራስ መተማመን።

# ክፍል ሦስት፡- ዓላማና ተልዕኮ

## 3.1 ዓላማዎች

3.1.1 የዐማራውን ነገድ ከፈጽሞ ጥፋት በመታደግ፣ እንደ ሰው፣ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ ሠርቶና በፈለገው አካባቢ ንብረት አፍርቶ መኖር እንዲችል፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ እንዲከበሩ ማድረግ፣

3.1.2 የዘረኛነትንና ፋሺስታዊ ሥርዓትን አራማጅ የሆነውን የትግሬ ወያኔን ቡድን አስወግዶ በምትኩ የሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ነገድና ጎሣዎች አንድነት፣ ነፃነት፣ ፍትሕ፣ ዕኩልነትና ሉዐላዊነት ማረጋገጥ የሚችል ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት መገንባት፤

3.1.3 የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና አካላት ለፍርድ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

3.1.4 የዐማራውን ኅልውና ከሚያከብሩ ነገዶችና ጎሳዎች ጋር በመተባበር፣ ዘረኛውን የትግሬ ወያኔ ሀገርና ሕዝብ ከፋፋይ ሕገመንግሥት አስወግዶ፣ በምትኩ በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚረቀቅና የሚጸድቅ ሕገመንግሥት መተካት፤

3.1.5 በሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ በሁሉም ዘርፎች ዐማራው ባለድርሻነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ማስቻል፤

### 3.2 ተልዕኮዎች

3.2.1 ዐማራውን ከፈጽሞ ጥፋት በመታደግ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ማረጋገጥ፤

3.2.2 በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ለዐማራውም ሆነ ለሌሎች ነገዶች የሥቃይና የመከራ ቋት የሆነውንና ኢትዮጵያን አደጋ ላይ የጣለውን የፋሺስት ወያኔ ትግሬ ነፃ አውጪ ግንባር፣ አምባገነን አገዛዝ ከሌሎች ለኢትዮጵያ አንድነት ከቆሙ ነገዶችና የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን ከሥልጣን ማስወገድ እና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመሥረት፤

3.2.3 በትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር ሁለንተናዊ የበላይነት የተመሠረተውን ሕገ-መንግሥትና በእርሱም አማካኝነት የሚራመደውን የዘር ፖለቲካ በመሻር፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት፣ ነፃነትና ፍትሕ ወዳድነት በሚያረጋግጥ ሕገመንግሥት መተካት።

# ክፍል አራት፡- ግብ

4.1 በሀገር ቤትም ሆነ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖረውን የዐማራ ነገድ ተወላጅ አደራጅቶ በመታገል የዐማራውን ኅልውና አስጠብቆ የኢትዮጵያን አንድነት ዕውን ማድረግ፣

4.2 ለኅልውናቸውና ለነፃነታቸው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለሚታገሉት የዐማራ ልጆች ትግል የሞራል፣ የገንዘብና መሰል ድጋፎችን በማስተባበር በዐኅኢአድ ሥር አደራጅቶና አዋቅሮ አንድ ጠንካራ የዐማራ ኃይል እንዲመሠረት ማድረግና የዐማራውን ኅልውና እውን ማድረግ።

4.3 በዐማራው የጎልውና እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ሕይዎታቸውንና አካላቸውን ላጡ ጀግኖች ቤተሰቦች አስፈላጊውን የመልሶ ማቋቋሚያ መርሓ ግብር መዘርጋት።

4.4 ለዐማራው ድምፅ የሚሆን ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንዲሁም ሌሎች የመረጃ ማስራጫ መንገዶችን ማደራጀትና ተግባራዊ ማድረግ።

4.5 የተቀናጀ የመረጃ ስብሰባና ጥንቅር በማካሄድ፣ ለነፃነት በሚደረገው ትግል የሚከፈለውን ልዩ ልዩ መስዋዕትነትና የጎላ አስተዋጽኦ ታሪክ ለመጪው ትውልድ መዝግቦ ማቆየት።

4.6 ላለፉት 26 ዓመታት በዐማራውና በሌሎች ጎሳዎች ላይ የደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል ዳግም እንዳይከሰት የሚያስችል የሰብአዊ መብት አስጠባቂ የጋራ መድረክ ወይም አካል መፍጠር።

4.8 የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል የፈጸሙትን ቡድኖችንና ግለሰቦችን ለፍርድ ማቅረብ።

4.9 በትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር የተመሠረተውን የመንግሥት ዓይነትና ቅርጽ እንዲሁም የዚሁ መሠረት የሆነውን ሕገ-መንግሥት በመሻር ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለሕዝቡ ዕኩልነት፣ ለብሔራዊ ጥቅማችን መከበርና ለሕዝቡ ሉዓላዊነት መረጋገጥ በቆመ ሕገመንግሥት መተካት።

4.10 በሁለንተናዊ መልኩ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመሥረት።

# ክፍል አምስት፦ ስልት

5.1 ለረጅም ዘመናት በውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ደራሲያን በዐማራው ላይ በሐሰት ታሪክ ላይ ተመሥርተው የተነዙትን የፈጠራ ጽሑፍች፣ አባባሎችና የተቀነቀኑ መፈክሮች ያዛቡትንና ያበላሹትን ፀረ-ዐማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ፣ በመረጃ ላይ ተመሥርቶ የተጠና ትክክለኛ ታሪክ በማቅረብ፣ የአጸፋ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሥራ በመሥራት ሐቁ ገሐድ እንዲወጣ ማድረግ፤

5.2 እውነተኛው የዐማራ ታሪክ ከሐሰቱ ተለይቶ እንዲወጣ በማድረግ፣ በሀገር ውስጥ በሌሎች ጎሳዎች በዐማራ ላይ የተሠራጨውን የሀሰት ፕሮፓጋንዳና ያሳደረውን ጥላቻ፣ እንዲሁም ምዕራባውያን በዐማራው ላይ ያሣደሩትን ጥርጣሬና የተሳሳተ ግምት ማስወገድ፤

5.3 ለዲሞክራሲዊ ዕኩልነት፣ ለሰላምና ብልጽግና በመፈቃቀድና በመከባበር ላይ ለተመሠረተ የሕዝብ ዕኩልነትና አንድነት መረጋገጥ ከቆሙ፤ በመርሕ ከሚገዙ ኃይሎች ጋር ልዩነቶችን በማጥበብ በመቻቻል በጋራ መሥራት፤

5.4 ብሔራዊ መግባባት እንዲኖርና በመተማመን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲቻል፣ ለብዙ ጊዜ ተጠይቆ በወያኔ ሤራ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለውን ሀገራዊ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ ብሔራዊ ዕርቅ -አውራጅ ጉባኤ ማካሄድ፤ ለዕርቁ ተግባራዊነትም ተከታይ ተግባራትን ማከናወን፤

5.5 በዓለም ዙሪያ ተበትኖ የሚገኘውን ዐማራ ለማደራጀት ዘመኑ የፈጠረውን ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ በየአካባቢው የዚህ ትግል ሐዋርያ ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦችን ማዘጋጀትና አስፈላጊውን ግንዛቤ (awareness) መፍጠር፤

5.6 ትግሉን በተገቢው ግብዓት ለመደገፍ እንዲያስችል የተለያዩ የገንዘብ ምንጮችን (financial resources) ማቋቋም፣ አስፈላጊውን ፖሊሲና የአፈፃፀም መመሪያ ማዘጋጀት፤

5.7 ድርጅቱ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚሆን ገቢ በቋሚነት የሚገኝባቸውን ዘዴዎች መተለም፤

5.8 የዐማራን ባለሙያዎች በሙያቸው እና በዕድሜአቸው አደራጅቶ ለዐማራው ኅልውና የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ማድረግ፤

5.9 የዐማራ ሴቶች የዐማራውን ኅልውና ለማስጠበቅ በሚደረገው ትግልም ሆነ በድኅረ ወያኔ የጎላ አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው እንዲደራጁ ማድረግ፤

5.10 የተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችንና መድረኮችን ማዘጋጀት።

# ክፍል ስድስት፡- ርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካዊ አቋም

## 6.1 ርዕዮተ ዓለም

የኢትዮጵያ መፃኢ የፖለቲካ ሥርዓት የሚወሰነው የትግሬ ወያኔ በሚወገድበት ሁኔታ፣ በወቅቱ የሀገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ምንነትና የኃይል አሰላለፍ ላይ ነው። በመሆኑም ዐኅኢአድ በዚህ የኃይል አሰላለፍ ውስጥ የጎላ ጥንካሬ ይዞ በመውጣት የዐማራውን ሕዝብ ጥቅሞች በበለጠ ከማስከበር ጎን የኢትዮጵያ አንድነት የሚረጋገጥበት ፖለቲካዊ መደላድል እንዲመቻች የበኩሉን ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል። ስለሆነም ዓለም ዛሬ ከምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት፣ የዐማራውን ኅልውና አስጠብቆ የኢትዮጵያን አንድነት ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ፣ **የሊበራል ዴሞክራሲን ርዕዮተ-ዓለም** መከተል ተገቢ ነው ብሎ ዐኅኢአድ ያምናል። ሆኖም ግን ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና በረጅም ታሪኳ ከገነባቻቸው መልካም ዕሴቶች በመነሳት ለዕድገት አጋዢ የሆኑ ሌሎች አሠራሮችና ግንኙነቶች እየተጠኑና እየተመዘኑ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዐኅኢአድ የሚጠበቅበትን ሁሉ ያደርጋል።

## 6.2 የፖለቲካ አቋም

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገሩ ላይ በተለያዩ ጊዜያት የተከፈቱበትን የቅኝ ግዛት ሙከራዎችና ወረራዎች ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ የሀገሩን አንድነትና ሉዐላዊነት ለማስከበር ወደ ኋላ ያላለውን ያህል፣ ለፍትሕ፣ ለዕኩልነት፣ ለማኅበራዊ ሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል። በዚህ ረገድ የዐማራ ነገድ ተወላጆች የለውጥ ሐዋርያና መሪ በመሆን በትግሉ ውጣውረድ ውስጥ ከፍተኛውን ሞትና እንግልት ተቀብለዋል።

እውነተኛው ታሪክ ይህ ሆኖ እያለ፣ የትግሬ ወያኔ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ታግዞና ወቅት ረድቶት መላ ኢትዮጵያን በ1983 ዓ.ም. ሲወርና የሽግግር መንግሥት ተብዬ መሠረትሁ ሲል፣ የዐማራን ነገድ ሆን ብሎ በማግለልና በጠላትነት በመፈረጅ ከሽግግር መንግሥት ምሥረታው እንዳይሳተፍ ከመደረጉም በላይ፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት እየፈፀመበት ይገኛል። ለከፋ እንግልትና ስደትም ዳርጎታል። በአጥቃላይ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቀዋል። በመሆኑም ለእነዚህና ለመሳሰሉት ውስብስብ የሀገሪቱ ችግሮችና ለዐማራ ነገድ ኅልውና መረጋገጥ አስተማማኝ የሆነና ሁሉ አቀፍ የሕዝብ ተሳትፎ ያለበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት መዘርጋት የግድ ይላል። የሚመሠረተው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓትም የሚከተሉትን መሠረታዊ መትከሎች ያቀፈ እንዲሆን ዐኅኢአድ ይታገላል።

6.2.1 የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት፣ የግለሰብ ነጻነትና የግል ሀብት የተከበረበት፣

6.2.2 የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ የሆነበት፣ ባለሥልጣኖች ሥልጣናቸው በሕግ የተገደበበትና ለሕዝብ ተጠያቂ የሚሆኑበት፣

6.2.3 የመንግሥትን ሥልጣን በሕዝብ ነፃ ተሳትፎ በረቀቀና በፀደቀ ሕግ-መንግሥት የሚመራበት፣

6.2.4 አወዛጋቢ ለሆኑ የፖለቲካ የውስጥ ችግሮች ብሔራዊ አንድነትንና ሉዐላዊነትን ሳይጋፉ ሕገ - መንግሥትና ሕዝበ-ውሳኔ መሠረት ያደረገ መፍትሔ የሚፈለግበት፣

6.2.5 ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት ዕኩል የሚሆኑበት፣

## 6.3 የመንግሥት ቅርጽና ተግባር

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ያለውን ታሪክ፣ ዕምነትና ባህል ከማዳበር ጎን ለጎን፣ ዜጎች በተናጠልና በጋራ ያላቸውን ቋንቋ፣ ባህልና ወግ የመጠቀምና የማበልጸግ መብታቸውን እንዲያከብር፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ሙሉና ቀጥተኛ የመሳተፍ መብቱን የሚያረጋግጥ፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነትና ሉዐላዊነት የሚያረጋግጥ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲኖር ዐኅኢአድ በጽኑዕ ይታገላል። በዐኅኢአድ ዕምነት የመንግሥት ቅርጽና ተግባር የሚከተሉት እንዲሆን ይጥራል፡፡-

6.3.1 የመንግሥት አደረጃጀትና ቅርጽ የዓለም ማኅበረሰብ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመን ታሪኩ ካካበታቸው መልካም የወል ዕሴቶቹን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሆኖ፣ ያሉት አማራጮች በግልጽ ለሕዝቡ ቀርበውለትና ተወያይቶባቸው በሚሰጠው ሕዝበ ውሳኔ መሠረት እንዲሆን ይታገላል፤

6.3.2 የሥልጣን ኃላፊነት በሚወጣው ሕገመንግሥት የሚወሰን ሆኖ፣ የሥልጣን ቦታዎች በዕወቀትና በችሎታ በውድድር መያዝ እንዳለባቸው ያምናል፤

6.3.3 የማዕከላዊው መንግሥት የሥልጣን አካላት እርስ በራሳቸው ቁጥጥርና ሚዛን የሚጠባበቁ ሦስት አካላት ይኖሩታል። እነርሱም ሕግ አውጭ፤ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ ናቸዉ።

6.3.4 እነዚህ ሦስት አካላት አንዱ በሌላው ሥራ ጣልቃ እንዳይገባ ሆኖ፣ በሕገመንግሥቱ የተገለጹ መብቶች፣ ጥቅሞችና ነፃነቶች ያላንዳች መሸራረፍ ዕውን እንዲሆኑ፣ የየበኩላቸውን የሕዝብ ተጠሪና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ሕገመንግሥቱ በሥራ እንዲውል የሚያደርጉ ይሆናል።

6.3.5 በሥልጣን አካላት መካከል የሕገ አተረጓጎም ችግር ሲከሰት፣ በሕገመንግሥቱ፣ ሕግ የመተርጎም ሥልጣን ያለው አካል በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም ይደረጋል። ለሁሉም የሥልጣን አካላት የሥልጣን ምንጭ የሚሆነው ሕገመንግሥት በሕዝበ ውሳኔ የሚጸድቅ ይሆናል፤

6.3.6 ሕግ አውጭው ክፍል በሕግ የተደነገገ ሥልጣንና ኃላፊነት ያላቸው ሆኖ፣ በሕዝብ በቀጥታ የሚመረጡ የሕዝብ ተወካዮችና የሕግ መወሰኛ አካሎች ይኖሩታል፤

6.3.7 የሕግ መወሰኛ አካሎች በሕገመንግሥቱ በሚወሰኑ አስተዳደራዊ መልክዓምድሮች የሕዝብ ብዛት መሠረት በሕዝብ ምርጫ የሚወከሉ ሰዎች የሚገኙበት ይሆናል፤

6.3.8 የሕዝብ ተወካዮች ቁጥር በእያንዳንዱ አስተዳደርዊ መዋቅር ማለትም ወረዳ ወይም ቀበሌ በሚኖረው የሕዝብ ብዛት መጠን በየጊዜው በሚሠራ ቋሚ ቀመር መሠረት የሚሰላ ይሆናል፤

6.3.9 ሕግ ተርጓሚው ክፍል ከሕግ አስፈጻሚውና ከሕግ አውጭው ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ፣ ተግባርና ኃላፊነቱን የሚያከናውነው በሕግ ብቻ ይሆናል፤

6.3.10 በየደረጃው በሕግ ተርጓሚነት የሚመረጡ ሰዎች የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ሊሆኑ አይችሉም፤

6.3.11 የሕግ አስፈፃሚው አካላት የሥልጣን ገደብና የቆይታ ጊዜ በሕግ የሚደነገግ ይሆናል። ያም ሆኖ ሕግ ተርጓሚው ተጠሪነቱን የሕዝብ ሆኖ፣ ሥልጣንና ኃላፊነቱን በአስፈጻሚው የማይነጠቅ ጠንካራ ሥልጣን እንዲኖረው ይደረጋል፤

6.3.12 በየደረጃው የሚገኙ ሕግ ተርጓሚዎች የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ የማመዛዘን ብቃትና ችሎታ ግምት ውስጥ ገብተው፣ እነዚህን አሟልተው የሚገኙ ግለሰቦችን አጣርቶ የማቅረብ ሕገመንግሥታዊ መብት በተሰጠው አካል ለውሣኔ ለሕግ መምሪያና ለሕግ መወሰኛ አካላት ቀርበው፣ በሁለቱ አካሎች የጋራ ስብሰባ በሕገ መንግሥቱ በሚደነገገው መሠረት ተገቢውን ድምፅ ያገኙት ቦታውን እንዲይዙ ይደረጋል፤

6.3.13 ሕግ አውጭ አካላትና የሀገሪቱ መሪ፣ በቀጥታ፣ በሚስጥርና በወቅታዊ የምርጫ ሂደት በሕዝብ የሚመረጡ ይሆናል። የሥልጣን ዘመናቸው በሕገ መንግሥቱ በሚደነግገው መሠረት ይሆናል፤

6.3.14 በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት ቢሮክራሲ አካሎች ምደባ በሙያ ብቃት ላይ በተመሠረተ ውድድር ይሆናል። ለሚሠሩት ሥራም ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ በሕግ የሚደነገግ ይሆናል፤

6.3.15 የፖሊስ፣ የሀገር መከላከያና የፀጥታ ኃይሉ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ግንኙነትና ቁርኝት የሌላቸው ሆነው፣ ዋና ተግባራቸው በሕገመንግሥቱ በግልጽ የሚጠቀሱትን የሀገሪቱን ዳር ድንበር ማስከበር፣ የሕዝቡን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ፣ የሕዝቡን ሰላምና ደኅንነት ማስጠበቅና ማረጋገጥ ይሆናል፤

6.3.16 የሕዝቡን የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሀሳቡን በነፃ የመግለጽ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች የተረጋገጡና የተከበሩ ከማድረግ ጎን፣ የብዙኃን መገናኛ መሣሪያዎች ያለአንዳች ገደብ የሙያና ሞራላዊ ግዴታቸውን በመጠበቅና ሕገመንግሥቱ በሚደነግገው አግባብ መሠረት፣ የሕዝቡን ፍላጎትና መሆን የሚሻውን በነፃነት ኢንዲያሰራጩ ሕጋዊ ዋስትናና ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

# ክፍል ሰባት፡- የዜጎች መብቶች

## 7.1 ሰብአዊ መብቶች፤

ሰብአዊ መብቶች፣ የሰው ልጆች ሰው በመሆናቸው ብቻ በተፈጥሮ ያገኟቸው መብቶች በመሆናቸው በመንግሥት እንዳይገደቡ ዐኅኢአድ ያላቋረጠ ትግል ያደርጋል። ለዚህም፡-

7.1.1 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ካውንስል እና የአፍሪቃ ኅብረት ያወጧቸው የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ሁሉ ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ዐኅኢአድ ይሻል፤ ለተግባራዊነቱም ይታገላል፤

7.1.2 የማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል የመሆን መብት ሳይሸራረፍ የሚከበር ይሆናል፤

7.1.3 የሁሉም ዜጎች ሰብአዊ መብቶች በምንም ሁኔታ ቢሆን በሕግ የተጠበቀ ይሆናል፤

7.1.4 የሁሉም ዜጎች ማኅበራዊ ደኅንነትና የሥራ ዋስትና በሕግ ተረጋግጠው ሳይሸራረፉ የሚከበሩ መብቶች ይሆናሉ።

## 7.2 ዴሞክራሲያዊ መብቶች

የትግሬ ወያኔ ፋሺስታዊ ቡድን ከተወገደ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመሠረተው መንግሥት የዜጎችን ዴሞክራሲያና ፖለቲካዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲያከብር ዐኅኢአድ ይፈልጋል፤ ለዚህም ተግባራዊነት የራሱን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። ይህም ማለት፦

7.2.1 የዜጎች የመናገር የመደራጀት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች በሕግ ተረጋግጠው ሕጋዊ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ዐኅኢአድ ይታገላል፤

7.2.2 ያለብዙኃን መገናኛ ነፃነት መከበር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኗል ማለት አይቻልምና ብዙኃን የመገናኛ አውታሮች ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ ሆነው ሕዝቡ በነፃነት በመንግሥት ላይ ያለውን አቋም የሚገልጽባቸው የመገለገያ መሣሪያዎች ይሆናሉ።

7.2.3 የፖለቲካ ሥርዓቱ የሊበራል ሥርዓትን ተከትሎ የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ሥርዓት መኖርን የተቀበለ ሆኖ ከገዥ ፖለቲካ ፓርቲው ውጭ ያሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች/ፓርቲዎች ሕጋዊ ዕውቅናና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ዐኅኢአድ ይታገላል።

## 7.3 የሃይማኖት ነፃነትና ዕኩልነት

7.3.1 መንግሥት በሃይማኖት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዳይገባ፣ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ በሕግ ይደነገጋል።

7.3.2 ሁሉም ሃይማኖቶች፣ አምልኮቶችና ኢ-አማንያን በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ የመከባበር መንፈስ አዳብረው አብረው እንዲኖሩ ጥረት ይደረጋል።

7.3.3 ሁሉም ሃይማኖቶች የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ በማያውክ አኳኋን በነፃነት የአምልኮ ሥርዓታቸውን እንዲያካሄዱ ይሆናል።

7.3.4 ማንኛውም ዜጋ በሃይማኖት የማመንም ሆነ ያለማመን ነፃነቱ በሕግ የተከበረ ነው።

## 7.4 የነገዶችና የጎሣዎች እኩልነት

7.4.1 በመርሕ ደረጃ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ነገዶች እና ጎሣዎች የሀገራችን የብዝኃነት መገለጫ ሀብቶች በመሆናቸው፣ ልዩነቶቹ ውበቶቻችንና የአንድነታችን ዕሴቶች ናቸውና የምንመካባቸውና የምንኮራባቸው ሀብቶች ናቸው፤

7.4.2 ነገዶችና ጎሣዎች የየራሳቸዉን ቋንቋ፤ ባህል፤ ሃይማኖት፤ ወግና ታሪክ ጠብቀው በእኩልነትና በመፈቃቀድ እንዲያዳብሩ የሚደረግ ሲሆን፣ የሁሉም የወል መገለጫ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ላይ የተመሠረተ አንድነትን በማጎልበት በጋራ አብረው የሚኖሩበትን ሀገር እንዲያሳድጉና እንዲያበለጽጉ የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

7.4.3 በመርሕ ደረጃ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥር ከአገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር አንፃር ከፍተኛ ቁጥር ሲኖረውና ይህን እንዲያረጋግጥ በሕገመንግሥቱ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሲወስን ብሔራዊ (ሀገራዊ) ቋንቋ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ እንዲመቻች የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ዐኅኢአድ ቢያምንም፣ የዐማራኛ ቋንቋ ካለው ታሪካዊ ዕሴት፣ የዕድገት ደርጃ፣ ለመማር፣ ለመናገርና ለኅትመት ካለው አመችነት አኳያ በመነሳት የኢትዮጵያ ብሔራዊ (የሥራ) ቋንቋ እንዲሆን ይጥራል። [የንጽጽሩ መጠን በሕገ መንግሥት የሚደነገግ ይሆናል።]

7.4.4 ለፖለቲካ ሥልጣን ተብሎ በነገድና በሃይማኖት ጥላቻ የተደራጁና ለመደራጀት የሚፈልጉ ቡድኖችና ግለሰቦች እንቅስቃሴ በሕግ ፈጽሞ የተከለከለ ይሆናል።

# ክፍል ስምንት፡- የኢኮኖሚ ጉዳዮች

የትግሬ ወያኔ ቡድን ሥልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ የሕዝባችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እጅግ እየከፋ መጥቷል። የትግሬ ወያኔ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመዳፉ ውስጥ በማስገባት ሌላውን የበይ ተመልካችና የዕለት ዳቦውን ለማግኘት ሲል የእርሱ ተግዥ አድርጎታል። በተለይም ደግሞ ይሄው አረመኔ የትግሬ ወያኔ ቡድን "የዐማራን ነገድ በኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያን በዐማራ ነገድ" እያቀያየረ ዐማራው ጭራሽ ከነባር ርስቱ፣ ሀብቱና ንብረቱ፣ ትዳሩና ቀየው ተነጥሎ እየተገደለና እየተሳደደ በስቃይ ላይ ይገኛል። ዐማራ ሆኖ መወለድ ወንጀል ሆኖ በሚያስገድልበትና ሀብት ንብረትን አስነጥቆ በሚያስባርርበት ሁኔታ የኢኮኖሚ ዕድገትና ተጠቃሚነት ጭራሽ የሚታሰብ አይደለምና ከሁሉም በፊት የሕብረተሰቡ የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ ወሳኝ ነው። በሌላ አገላለፅ የዜጎች ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበት ሁኔታ ውስጥ ስለኢኮኖሚ ግንባታ ማውሳት አሁንም የወያኔን ዘራፊነት እውቅና ሰጥቶ ማስቀጠልና ወያኔ እየዘረፈ ላለው የውጭ ዕዳ ራስን ተጠያቂ አድርጎ እንደማቅረብ ይወሰዳል። ይህን መድሎአዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመለውጥ ከላይ በጥቅሉ የተቀመጡ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጋር የተቆራኘ ነው ብሎ "የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት" ከልብ እያመነ፣ በሕገወጥ መንገድ የተወረሱ (የሀገርም ይሁን የግለሰብ ንብረቶች) የገጠርም ይሁን የከተማ ቦታዎች፣ ቤቶችና መደብሮች ወደፊት ሕግን መሠረት አድርገው እንዲታዩ ዐኅኢአድ የራሱን ሚና ይጫወታል።

የዐኅኢአድ የኢኮኖሚያዊ መርሆዎችና ፖሊሲዎች በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርሕ የሚገዛ ሆኖ፣ በኢኮኖሚ መስክ የሚከተሉት ዕውን እንዲሆኑ ይታገላል።

8.1 የኢኮኖሚ ነፃነት የሚከበርበትና የዜጎች ሁሉ የኑሮ ደረጃ የሚሻሻልበትን ፖሊሲ በመንደፍ፣ የሀገርና የሕዝብ ሀብት በሚያሳየው የፍላጎትና አቅርቦት ሚዛን እየተመራ በነፃ ገበያ ሥርዓት ላይ የቆመ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገቶች የሚጣጣሙበት፣ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የሚፈጥር የሕዝብ አስተዳደር ይመሠረታል፤

8.2 መንግሥት በጥናትና ምርምር ግኝቶች ላይ ተመሥርቶ ሀገሪቱ ራሷን የመመገብ አቅም እንዲኖራትና ሕዝቡ በሥራ ተሠማርቶ የኑሮ ደረጃውን የሚያሻሽልበትንና ወደፊት የሚያይ ሀገራዊ ዕቅድ በየአምስት ዓመቱ ይፋ ያደርጋል፤

8.3 በግልም ሆነ በጋራ ተቋማት የምርት፣ የንግድና የአገልግሎት ተግባራትን ለሚያከናውኑ የኢኮኖሚ ኃይሎች መንግሥት የተጠናና ሕጋዊ መሠረት ያለው የማበረታቻ ድጋፍና አገልግሎት ይሰጣል፤

8.4 ለሀገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም የሚሰጠው የቅድሚያ ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማናቸውም የኢኮኖሚ መስክ ለሕዝባዊ ልማት ቅድሚያ ፈቃድና ድጋፍ የሚሰጠው ለሀገሪቱ ዜጎች ይሆናል። የውጭ መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች በኢኮኖሚው መስክ ለራሳቸው ጥቅምና ለሕዝብ ብልጽግና ይሠሩ ዘንድ፣ በግልም ሆነ በማኅበር ወይንም በሽርክና የሚሳተፉበት ሥርዓት ይዘጋጃል።

8.5 በመዋዕለ ንዋይ እጥረትም ሆነ በሀገር ውስጥ የገበያ ፍላጎት ማነስ ምክንያት ዜጎች ሊሠማሩባቸው በማይችሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የውጭ ዜጎች ወይም ኩባንያዎች እንቅስቃሴ እንዲያደርጉና ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር አስፈላጊውን ፖሊሲና የአፈጻጸም መመሪያ ይቀርጻል፤

8.6 መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተፈጥሮ ፀጋና የጋራ ሀብት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለእያንዳንዱ ዜጋ ያለአድልዖና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በባለቤትነት የያዘውን የገጠር መሬት ወይንም የከተማ ቦታ የግሉ የማድረግ የመሸጥ፣ የመለወጥ ወይንም የማከራየት የማውረስና የማስተላለፍ ሙሉ መብቱ የተጠበቀ ሆኖ፣ የግል የባለቤትነት መብቱ የጸና ይሆናል፤

8.7 አርሶአደሩ፣ አርብቶ አደሩና ባለሀብቱ የጋራና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ፍትሃዊና ዘመናዊ የግብይት

ሥርዓት እንዲዘረጋና ከገበያ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ስልታዊ ተፅዕኖዎች የተላቀቀ እንዲሆንና የገበያ ሥርዓት በፅኑዕ እንዲሰፍን አበክሮ ይሠራል፤

8.8 ከአርሶአደሩ ይዞታ ውጪ የሆኑ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ላይ እንደ ሁኔታው አርሶ አደሮችን በቅድሚያ በግል ከዚያም እንደ አስፈላጊነቱ በማኅበር ተደራጅተው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዘው ከትንሽ መሬት ብዙ ማምረት እንዲችሉ እገዛ በማድረግ በሂደትም ራሳቸውን ወደ መካከለኛ ገቢና ባለሀብትነት እንዲሸጋገሩ ተገቢው ድጋፍ ማድረግ፤

8.9 የአርብቶ አደሩ ኅብረተሰብ የኑሮ ደረጃውን ማሻሻል እንዲችል የእንስሳት ሀብት አያዛዝና አጠቃቀም ዘዴ በማስተማር በቋሚነትም ሊሰፍር እንደሚችልና አስፈላጊ የሆኑ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶች እና የማኅበራዊ ተቋማት እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8.10 በግብርና ላይ የተሠማሩ አርሶአደሮችም ሆኑ የግል ባለሀብቶች በዘመናዊ ግብርና ግብይት ሥርዓት ግንዛቤ ያላቸው ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በቂ ሙያዊ ድጋፍ የሚያገኙበት አሠራር ይዘረጋል፤ ለገበያ ያላቸው ቅርበት የተሻሻለ እንዲሆንና የሥራቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

8.11 ኢኮኖሚያዊ መሠረተ ልማቶች [ውሃ፣ መንገድ፣ ባቡር፣ መብራት፣ ስልክ፣ ፖስታ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔት፣ ወዘተርፈ] ለገጠርም ሆነ ለከተማው ማኅበረሰብ አባላት ደረጃ በደረጃ እንዲዘረጋ ይደረጋል፤

8.12 የሀገር ውስጥም ሆነ የአለም አቀፍ ኢንቬስትመንት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መዋዕለነዋይ ግንባታና ጥንካሬ ወሳኝ በመሆኑ፤ ለኢንቬስተሮች የተቀላጠፈ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

8.13 በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥ የአገልግሎት ክፍል ኢኮኖሚው ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ይህ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲያድግ አመቺ የሆኑ ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ ይደረጋል፤

8.14 ለአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው መስፋፋት የሚያመቹ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ባለሀብቶች የንግድ ሥራ አገልግሎት የሚውሉ የገንዘብ ምንጮች እና ወይም የብድር ተቋማት እንዲኖሩ ጥረት ያደርጋል፤

8.15 አነስተኛ የንግድ ሥራዎች የኢኮኖሚው ዋና ሞተሮች እንዲሆኑ እና መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የነጋዴነት ሚና እንዳይኖረው ጥረት ያደርጋል፤

8.16 ሀገሪቱን ወደ ዘመናዊነት ለማሸጋገርና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ወደ ተሻለ ለመለወጥ ከግብርናና ከአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚው ሌላ የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲያድግ የተሻሻሉ ፖሊሲዎች እንዲኖሩ ጥረት ያደረጋል፤

8.17 ኢንዱስትሪውና ግብርናው በመመጋገብ እንዲያድጉና አንዱ የሌላውን ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያመች ፖሊሲ እንዲወጣ ጥረት ያደርጋል፤

8.18 የሀገሪቱን የገበያ ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ ትንንሽ የማምረቻ ተቋማት ወይም የጎጆ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ የሚያስችል ፖሊሲ እንዲኖር ያደርጋል፤

8.19 ሀገሪቱ ካላት የሕዝብ ብዛት ሀብት አንፃር ፈጣን እድገት ሊያመጡ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በጥናትና ምርምር እንዲለዩና ለባለ ሀብቶች ለኢንቨስትመንት ውሳኔ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፤

8.20 የመብራትና የቴሌኮም አገልግሎቶች፣ የገንዘብና የመድህን ሥራዎች ሀገርን በሚጠቅም መልኩ ለውድድር ገበያ ክፍት እንዲሆኑ የፖሊሲ አማራጮች እንዲኖሩ ይደረጋል።

# ክፍል ዘጠኝ፦ ማኅበራዊ ጉዳዮች

## 9.1 የትምህርት ፖሊሲ

ትምህርት የአንድ ሀገር የዕድገት መሠረት መሆኑ ይታመናል። ይሁን እንጂ፣ የትግሬ ወያኔ ሀገሪቱን ከወረረበት ጊዜ ጀምሮ በአንፃራዊ በጥራታቸውና ነፃነታቸው ይታወቁ የነበሩት የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት ጉዞአቸው የኋሊት በመሆኑ የአገሪቱ የትምህርት ጥራት በእጅጉ ወድቋል። ይህም በመሆኑ የሀገሪቱ የትምህርት ተቋማት የተሞሉት በወያኔ ካድሬዎችና የፖለቲካ ምልምሎች ስለሆነ ተማሪዎቹ ተገቢውና ዘመኑ ከሚጠይቀው ዕውቀት ተቋዳሽ ለመሆን አልቻሉም። የአካዳሚክ ነፃነታቸውን የሚሹ ምሑራንና ተማሪዎች ከትምህርት ተቋማትና ማዕከሎች እንደ ወፍ መባረራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሥርዓተ ትምህርቱ (ካሪኩለሙ) የኢትዮጵያን ዕውነተኛ ታሪክና ሀገሪቱ የምትሻውን የተማረ የሰው ኃይል ማፍሪያ ሳይሆን፣ ለወያኔ ሀገርና ሕዝብ ማጥፊያ ሁነኛ መሣሪያ እንዲሆን እየተደረገ ነው። ምንም እንኳን ቁጥራቸው አብላጫም ቢሆን፣ የአማርኛ ቋንቋ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ባልሆነበት አካባቢ የሚኖሩ የዐማራው ነገድ ተወላጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በዐማርኛ እንዳይማሩና እንዳይዳኙ መብታቸው ተነፍጓል። በመሆኑም "የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት" ይህንን ዐይን ያወጣና መድሎአዊ የትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ለሀገራችን ዕድገትና ሁሉም ዜጎች በችሎታቸውና በትምህርት ውጤታቸው ያለምንም አድልዖ የሚገነባ የትምህርት ተቋምና ፖሊሲ እንዲቀረጽ የራሱን ጉልህ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም የትምህርት ፖሊሲው የሚከተለውን እንዲሆን ዐኅኢአድ ያታገላል።፦

9.1.1 በሁሉም ደረጃ፣ ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽነት እንዲኖረው ለማረጋገጥ በጽናት ይታገላል፤

9.1.2 የሀገሪቱን የዕድገት አቅጣጫና የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በሚያስገባ ሁኔታ ሥርዓተ ትምህርቱ ዕሴት ተኮር እና ችግር ፈቺ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፤

9.1.3 የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች በነፃ ይሰጣሉ። የዩኒቨርሲቲ ትምህርት እንደየ ተማሪው አቅም እየተገመገመ በክፍያ፤ በድጎማና በነፃ መሰጠት የሚችልበት ሥርዓት በጥናት እንዲዘረጋ ይደረጋል፤ ለትምህርት ክፍያ የሚውል የብድር አገልግሎት እንዲኖር ይደረጋል፤

9.1.4 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሕጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

9.1.5 በተከታታይነት መማርንና ሙያ ማሻሻልን (Lifelong Learning) ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ማኅበራትን በማስተባበር ለሙያ ማሰልጠኛ እና ወይም ማሻሻያ፣ ለጥናትና ምርምር ተቋሞች መቋቋምና ማደግ የበኩሉን ጥረት የሚያደርግበት ሥርዓት ይገነባል።

9.1.6 በትምህርት ዙሪያ ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችና ምርምሮች እንዲደረጉና የጥናት ግኝትን መሠረት ያደረገና ከወቅቱ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት ዘርፍ ዕድገት እንዲፋጠን ይታገላል።

## 9.2 የጤና ፖሊሲ

9.2.1 የጤና ፖሊሲ በሽታዎችን በመከላከልና የበሺታ ምንጮችን በማስወገድ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል።

9.2.2 ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ የሌላቸው ዜጎች በሚወጣው የጤና ፖሊሲ መሠረት በነፃ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል።

9.2.3 ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣውን የሕክምና ዋጋ ለመሸፈንና የዜጎችን ጤንነት ለማሻሻል የኢኮኖሚ አቅምን ያገናዘበ ሀገራዊ የሆነ የጤና መድኅን እንዲኖር ያደርጋል፤ በሀገሪቱ ውስጥ የጤና መድኅን እንዲስፋፋም ተገቢውን ማበረታቻና እገዛ ያደርጋል።

## 9.3 የባህል ፖሊሲ

የትግሬ ወያኔ እኩይ ቡድን አባላት በባንዳ አባቶቻቸው አማካኝነት ከፋሺስት ሙሶሎኒ የወረሱትን ኢትዮጵያዊነትን የማፈራረስ መርሓግብር ተግባራዊ ለማድረግ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በሌሎች ነገዶችና ጎሳዎች በዐማራ ነገድ የተጫነባቸው ዕዳ አስመስሎ በመሳል፣ ከዐማራው ውጭ ያሉት ሌሎች ነገዶች ኢትዮጵያዊነትን እንዲጠየፉና እንዲሸሹ ከማድረጉም በላይ፣ በዐማራ ላይ በጠላትነት እንዲቆሙ አድርጓል። ይሁን እንጅ ኢትዮጵያ የተለያዩ ነገዶች ታሪካዊ ቁርኝት ውጤት መሆኗን በሚገባ በማስተማር ሁሉም ዜጎች ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ያለምንም አድልዖ እንዲያበለጽጉ የሕግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ዐጎኢአድ የበኩሉን ሚና ይጫወታል። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሁሉም ነገዶች ማንነት መገለጫ፣ የወል ቤት እንደሆነች ዐጎኢአድ በጽኑ ያምናል። እንዲሁም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ሊያግባባ የሚችል ሀገር - አቀፍ (ብሔራዊ ቋንቋ) ሊኖረን እንደሚገባም ዐጎኢአድ አበክሮ ያምናል።

በዚህ ረገድ ምንም እንኳን የትግሬ ወያኔ ፀረ - ዐማራ ቡድን በዐማርኛ ቋንቋ ላይ ከፍተኛ የማጥፋት ዘመቻ የከፈተ ቢሆንም ቅሉ፣ ዐማርኛ ቋንቋ አሁን ካለበት ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የደረሰው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥረትና አስተዋፅዖ ነው። በመሆኑም የዐማርኛ ቋንቋ ከተናጋሪው ብዛት፣ ከቋንቋው የዕድገት ደረጃና በቀላል ለመማር ካለው ምቹነት አኳያ ሲታይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ (የሥራ ) ቋንቋ ለመሆን መሥፈርቱን ሙሉ በሙሉ ያሟላ ነው ብሎ ዐጎኢአድ ያምናል፤ ይህም ተግባራዊ እንዲሆን ያለማሰለስ ይጥራል። እርግጥ ነው ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎች ማዕከል በመሆኗ የባህል ልዩነቶች የጋራ ሀገራችን ለሆነችው ኢትዮጵያ ጌጦች ናቸው ብሎ ዐጎኢአድ በጽኑዕ ያምናል። በመሆኑም ዜጎች ባህላቸውንና ቋንቋቸውን ያለምንም ተጽዕኖ እንዲያሳድጉና እንዲያበለጽጉ የሕግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ዐጎኢአድ የራሱን ሚና ይጫወታል።

## 9.4 ማኅበራዊ ዋስትና

በመርሕ ደረጃ ዐጎኢአድ ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ የሆነ ማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖር ይታገላል። ስለሆነም፦

9.4.1 የዜጎችን ማኅበራዊ ደኅንነትና ጤና ለመንከባከብ የሚያስችል የማኅበራዊ ዋስትና ተቋም እንዲቋቋም ይንቀሳቀሳል።

9.4.2 ሕፃናት፣ እናቶች (ነፍሰ ጡሮችና አጥቢዎች)፣ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል፤

9.4.3 ሀገሪቱን በመከላከያ ኃይል ሲያገለገሉ ጉዳት ለደረሰባቸው አርበኞች ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ይንቀሳቀሳል፤

9.4.4 በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ለወላጅ አልባነት የተዳረጉ ልጆች ልዩ እንክብካቤና ድጋፍ በማድረግ፣ ራሳቸውንና ማኅበረሰቡን መርዳት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲመቻች ይጥራል፤

9.4.5 የዜጎች ማኅበራዊ ዋስትና የማግኘት ሙሉ መብት እንዲረጋገጥ ይታገላል።

# ክፍል አሥር፦ የአገር መከላከያና የሕዝብ ደህንነት

ብሔራዊ የመከላከያ ኃይል፣ የፖሊስ ሠራዊትና ደኅንነት ጥበቃ የሀገሪቱን ዳር ድንበር፣ ሉዐላዊነት፣ ነፃነትና የውስጥ ጸጥታ የሚያስከብርና ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት በሆነ ዕምነት፣ ሞራልና ሥነ-ምግባር የሚታነጽና የሚመራ እንዲሆን ዐጎኢአድ ግልጽ አቋም አለው። የሀገሪቱ የመከላከያ ኃይል፣ የፖሊስ ሠራዊትና ደኅንነት የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዐላዊነት ለመጠበቅ እንጂ፣ በሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ ዕድሜ ለማራዘም መሆን እንደሌለበት ዐጎኢአድ በጽኑዕ ያምናል። ለዚህም፦

10.1 የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የፖለቲካ ወገንተኝነት የማይከተል፤ ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ ሕገመንግሥት ብቻ የሆነ፤ ተግባሩ ዳር ድንበር ማስከበር ብቻ ይሆናል።

10.2 በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጥሮ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ ያለውን አቅም በመጠቀም የሚደርሰውን ጥፋት ለመቀነስ

በሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት በሚደርሰው ጥሪ መሠረት የበኩሉን አስተዋጾዖ ያደርጋል።

10.3 ሰላም፣ ፀጥታና ሕግ አስከባሪ የፖሊስ፣ የደኅንነትና የፍርድ ተቋሞች ሙያና ሥራቸው በሕገመንግሥት የተደነገገ፤ የዜጎችን መብትና ነፃነት በሚያስከብር መልኩ የተቃኘ እንዲሆን ይታገላል።

10.4 የመከላከያ ሠራዊቱም ሆነ የፖሊስ፣ ደህንነትና የፍርድ ተቋማት በሕዝባዊ ድምፅ ብልጫ ተመርጦ አገሪቱን ከሚያስተዳድረው ፓርቲ ጋር ምንም ግንኙነት እንዳይኖራቸው ይደረጋል፤

10.5 የመከላከያ ሠራዊቱም ሆነ የፖሊስ፣ ደህንነትና የፍርድ ተቋማት አባላት እንደማንኛውም ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ መብት ቢኖራቸውም ተቋማቱ እንደተቋም በፖለቲካ ሥርዓቱ መለወጥ የሚለዋወጡ አይሆኑም። ስማቸውም ሆነ ተግባራቸው ብሔራዊ እንጂ የፓርቲ ተቀጥላ እንዳይሆኑ ይደረጋል።

# ክፍል አሥራ አንድ፡- የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከማንኛውም ዓይነት ጠብ አጫሪነትና ጣልቃ ገብነት የተቆጠበ፣ በማንኛውም የባዕድ ኃይል ተጽዕኖ ሥር የማይወድቅ፣ በሰላም አብሮ በመኖርና ብሔራዊ ጥቅምን በሚያስከብር መርሕ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ዐኅኢአድ ይታገላል።

ወያኔ በጉያው ደብቆ በያዘው ድብቅና ግልጽ ሤራ ወንድም ከሆነው የኤርትራ ሕዝብ ጋር ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመለያየት ያደረገው እኩይ አካሄድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ከውጭ ወራሪዎች ጋር ሕይዎቱን አሳልፎ ከሰጠበት ሁኔታና ከእውነተኛው ታሪክ አኳያ በማገናዘብ ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር የምትገናኝበት የባህር በር እንዲኖራት ሕጋዊ፣ ታሪካዊና ሰላማዊ መንገዶችን በመከተል ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኝ ዐኅኢአድ በግንባር ቀደምትነት ይጥራል።

11.1 የውጭ ፖሊሲ ማለትም ማናቸውም ዓይነት የውጭ ግንኙነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚያስከብር እና የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በሚያረጋግጥ መልኩ የተቃኘ እንዲሆን ያደርጋል፤

11.2 የተባበሩት መንግሥታት እና የአፍሪካ ቻርተር የሚደነግጉትና አገሪቱም የተስማማችባቸውን ውሎች ያከብራል፤

11.3 ከበለፀጉና በማደግ ላይ ካሉ ሀገሮች የሚኖረው ግንኙነት በገለልተኝነት መርሕ የሚገዛ እንዲሆን ይታገላል፤

11.4 ዐማራው ኅልውናውንና ብሔራዊ ማንነቱን ለማረጋገጥ በሚያደርገው ትግል ውስጥ፣ እስከ ዛሬ በጠላትነት ፈርጀው ዛሬ ለሚገኝበት ሁኔታ ካደረሱት አገሮችና ቡድኖች፣ የዐማራውን ዕውነተኛ ማንነት በተከታታይ በልዩ ዲፕሎማሲያዊ ትግል በማድረግና በማስረዳት ጠላትነታቸውን አርግበው አጋር ሊሆኑ የሚችሉበትን ሥራ በመሥራት ዐማራው ብዙ ወዳጆች እንዲኖሩት ይጥራል፤

11.5 በሃይማኖትም ሆነ በሌላ መልኩ ተደራጅተው ዓለምአቀፋዊ የሽብር ተግባር የሚፈፅሙትን ለመታገል ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሀገሮች እና/ወይም ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

**መጋቢት 2009 ዓም**